**ቅጽ 23 ቁጥር 2**

## የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የሁለት አቅመ ደካማ ነዋሪዎች መኖሪያ ቤቶችን በማደስ ላይ ይገኛል፡፡

የኢትዮጵያ መድን ድርጅት አቅመ ደካሞችን ለመርዳት በማሰብ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 03 የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር አቶ ሐብታሙ ኃ/ሚካዔል፣ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ነፃነት ለሜሳ፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የበላይ አመራር አባላት በተገኙበት የሁለት አቅመ ደካማ ነዋሪዎችን መኖሪያ ቤቶች እድሳት ነሐሴ 01 ቀን 2013 ዓ.ም አስጀመረ፡፡





ድርጅቱ ማህበራዊ ኃላፊነትን ከመወጣት አንፃር ብዙ ስራዎችን ሲሰራ ቆይቷል፡፡ ለአብነት ያህል መቄዶንያ የአረጋውያንና የአእምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከል፣ የኢትዮጵያ አይነስውራን ማህበር፣ እውን በጎ አድራጎት ማህበር፣የኢትዮጵያ ማየትና መስማት የተሳናቸው ማህበር፣ የተማሪዎች የምገባ አገልግሎትና የመሳሰሉት የሚጠቀሱ ሲሆን በዘንድሮ ክረምትም የሁለት አባወራ አቅመ ደካሞች መኖሪያ ቤቶችን እድሳት በማስጀመር ማህበራዊ ኃላፊነቱን በመወጣት ላይ ይገኛል፡፡

በክረምት የአቅመ ደካሞችን ቤቶች መጠገን ከዚህ በፊት በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አቢይ አህመድ እና በተለያዩ የመንግስት ባለስልጣናት የተጀመረ ቢሆንም ሁሉም የመንግስትና የግል ድርጅቶች እንዲሁም ባለሀብቶች በአቅመ ደካሞች መኖሪያ ቤት እድሳት ላይ ቢሳተፉ የብዙሃኖቹን የቤት ችግር ማቃለል ይቻላል በሚል መንፈስ የተነሳሳው የኢትዮጵያ መድን ድርጅትም ከብር 150,000 በላይ በመመደብ እድሳቱን ለማከናወን አስጀምሯል፡፡



የቤት እድሳት አጀማመር በከፊል

የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ነፃነት ለሜሳ፣ እንደተናገሩት ከዚህን በፊትም ድርጅታችን የተለያዩ ማህበራዊ ስራዎችን ሲሰራ የቆየ መሆኑን ጠቅሰው፣ አሁን ያስጀመሩት የአቅመ ደካሞች መኖሪያ ቤት ግንባታ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተሰርቶ እንደሚጠናቀቅና ባለቤቶቹ እንደሚረከቡ እና ለወደፊቱም እንደዚህ አይነቱን ስራ ለማከናወን ወደ ኃላ እንደማይሉ ገልፀዋል።

## <u>የሰንደቅ አላማ ቀን በኢ.መ.ድ. ተከበረ</u>

አስራ አራተኛው የሰንደቅ አላማ ቀን በኢትዮጵያ መድን ድርጅት ዋና መስሪያ ቤት የተከበረ ሲሆን አቶ ነጻነት ለሜሳ የኢ.መ.ድ. ዋና ሥራ አስፈጻሚ ከመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኃላፊዎች የበላይ ስራ አመራር አባላት ዳይሬክቶሬቶች የዋናው መ/ቤት ሠራተኞች እንዲሁም የማዕከላዊና የህይወት አዲስ ዲስትሪክት ዳይሬክተሮችና እና ሠራተኖች በተገኙበት በጋራ ተከብሯል።



*የበዓሉ አከባበር በከፊል*

የበዓሉን መከበር አስመልክቶ አቶ ነጻነት ለሜሳ የኢ.መ.ድ. ዋና ሥራ አስፈጻሚ ንግግር ያደረጉ ሲሆን በንግግራቸውም 14ኛው የሰንደቅ ዓላማ ቀን ልዩ መሆኑን የገለጹ ሲሆን ልዩ ከሚያደርገው ውስጥ በበጀት ዓመቱ ሃገራዊ ምርጫ ተደርጎ የሃገሪቱ ህዝብ የወደደውን ወይም የመረጠውን መንግስት በካርዱ ብቻ የመረጠበትና አዲስ መንግስት ምስረታ የተከናወነበት ማግስት መሆኑና ከዚህ በተጨማሪም የኢትዮጵያ ታላቁ የህዳሴ ግድብ ሁለተኛ ዙር የውሃ ሙሌት በድል መጠናቀቅ በኋላ የተከበረ በመሆኑ ነው ብለዋል። በመጨረሻም የኢትዮጵያ ህዝብ መዝሙር በህብረት ከተዘመረ በኋላ የበዓሉ መርሃ ግብር ተጠናቋል።

# ልዩ ልዩ

## ሚዛኑ

አንድ ቅቤ አምራች ገበሬና ዳቦ አምራች ነጋዴ እንደ አጋጣሚ ድግስ ላይ ተገናኝተው ያወራሉ። በጨዋታቸው በጣም ስለተግባቡ ከዚህ በኋላ አጋጣሚ ፈጥረው ለመገናኘት ይስማማሉ። ዳቦ አምራች ነጋዴው ጠዋት ጠዋት 300 ግራም ዳቦ ሲልክለት ቅቤ አምራች ገበሬው ደግሞ ማታ ማታ 300 ግራም ቅቤ ሊልክለት ተስማሙ።

በዚህ መልኩ ብዙ ጊዜ ከቆዩ በኋላ የዳቦ ነጋዴው የቅቤ መጠን እየቀነሰ መሄዱን አየ። በመጨረሻም ሚዛን ላይ ሲያስቀምጠው 150 ግራም ሆኖ አገኘው። በዚህም በጣም አዘነ፤ ተበሳጨም። ቅቤ አምራች ገበሬውንም አስጠራው። ሌሎች ሰዎች እንዲያዳምጡት አድርጎ ‹ከተስማማነው ውጭ የቅቤውን መጠን ለምን ቀነስከው?› ሲል ጠየቀው። ገበሬውም ‹እኔ ፈጽሞ አልቀነስኩትም› ሲል በአግራሞት መለሰ። ነጋዴውም ቅቤውን በሚዛን ለክቶ አሳየው። 150 ግራም ነው። ገበሬውም አዘነ። ‹እኔ ቤት ውስጥ የ300 ግራም መለኪያ የለኝም። አንተ ጠዋት ዳቦውን ስትልክልኝ በእጅ ሚዛኑ አንደኛው ሰሐን ላይ አደርገዋለሁ፤ ከዚያም ቅቤውን በሌላኛው ሚዛን አስቀምጠዋለሁ። ልክ ከዳቦው ጋር እኩል ሲመዝኑ በዕቃ አዘጋጅቼ እልክልሃለሁ› አለው። ወዲያውም ጠዋት የላከለትን ዳቦ አውጥቶ ሚዛኑ ላይ አስቀመጠው። ዳቦው 150 ግራም ነበር የሚመዝነው። ነጋዴው አፈረ።



‹የምታገኘው ለሌላው ባደረግከው ልክ ነው፡፡ 150 ሰጥተህ 300 ልታገኝ አትችልም፤ እባብ ሰጥተህ ርግብ፣ ድንጋይ ሰጥተህ ዳቦ፣ እሬት ሰጥተህ ማር ልታገኝ አትችልም፤ አንተ ብቻ ብልጥ ልትሆን አትችልም፤ ማሾውን አጥፍተህ ብርሃን ልታገኝ አትችልም፤ ሌላው ገድለህ አንተ በሰላም ልትኖር አትችልም› አለው ገበሬው፡፡

ማንኛውም ድርጊት ተመሳሳይና ተመጣጣኝ የሆነ ምላሽ አለው፡፡ አንተ እዚህ ለብቻህ ቤትህ ውስጥ ሆነህ ክፉ ስታደርግ ሌላውም በቤቱ ብቻውን ሆኖ ክፉውን ይመልስሃል፡፡ ‹እዛም ቤት እሳት አለ› እንዳሉት ነው አለቃ ገብረ ሐና፡፡ አንተ ጎመድ ይዘህ ከወጣህ ሌላውም አያቅተውም፤ አንተ ገጀራህን ከሳልክ ሌላውም ይስላል፤ አንተ የሌላውን ወገን ስታፈናቅል፣ ያኛውም ያንተን ወገን ያፈናቅላል፡፡ ዛፍ ቆርጠህ ዝናብ፣ በካይ ጋዝ እየለቀቅክ የተስተካከለ የአየር ንብረት አትጠብቅ፡፡ ተፈጥሮም በሰጠሃት መጠን ነው የምትመልስህ፡፡ በዓለም ላይ ሚዛኑ አንድ ነው፤ ተመዛኞቹ ግን ይለያያሉ፡፡ እዚህ ካጎደልክ፣ እዚያም ያጎድሉብሃል፡፡ እዚህኛው ዩኒቨርሲቲ የዚያኛው ልጅ አለ፤ እዚያኛው ዩኒቨርሲቲም የአንተ ልጅ ይገኛል፡፡ እዚህ የአንተ ወገን ብዙኃኑን ይዟል፣ እዚያ ግን አናሳ ነው፡፡ እዚህ አናሳ የሆነው ደግሞ እዚያ ብዙ ይሆናል፡፡ የብዙኃን ወገን በሆንክበት ቦታ አናሳው ካሰቃየህ፣ አናሳ በሆንክበት ቦታ ደግሞ ብዙኃን ያሰቃዩሃል፡፡ እዚህ ባለ ሥልጣን እንደሆንከው እዚያ ተራ ትሆናለህ፡፡ የሚያዋጣው በሚዛኑ ልክ ትክክለኛውን ማድረግ ብቻ ነው፡፡

*የዳንኤል ክብረት እይታዎች ድህረ ገጽ ላይ (እ.ኤ.አ. ታህሳስ 7 ቀን 2019 የተለጠፈ)*

## ሠራተኛ ነክ ዜናዎች

### የተሠጡ ስልጠናዎች

የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ለተለያዩ የድርጅቱ ሠራተኞች እ.ኤ.አ ከጥቅምት 1 ቀን እስከ ታህሣስ 31 ቀን 2021 ድረስ በጠቅላላ መድን ጽ/ቤት፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሰርቪስ ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ በዚህም መሠረት፡-

### በኢትዮጵያ መድን ድርጅት የተሰጡ ስልጠናዎች

- እ.ኤ.አ. ከህዳር 12- 16 ቀን 2021 ከድርጅቱ መዋቅር ጋር የተያያዘ ለ ለ 60 የዲስትሪክትና ቅርንጫፍ ሠራተኞች ስልጠና ተሰጥቷል።
- እ.ኤ.አ. ከህዳር 24- 25 ቀን 2021 የድርጅቱን መዋቅር ለመተግበር የሚያስችል ስልጠና ለ 60 ሠራተኞች ተሰጥቷል።
- እ.ኤ.አ. ከታህሳስ 7- 8 ቀን 2021 "**fire insurance**" ለ 2 ሠራተኞች ስልጠና ተሰጥቷል።
- እ.ኤ.አ. ከጥቅምት 25- 29 ቀን 2021 ለሰባት ሰራተኞች እንዲሁም እ.ኤ.አ. ከህዳር 15-19 2021 ለ11 ሠራተኞች እና ከታህሳስ 27-31 ለ 8 ሠራተኖች "**property and pecuniary insurance**" ስልጠና ተሰጥቷል።
- እ.ኤ.አ. ከጥቅምት 25- 29 ቀን 2021 ለ 7 ሰራተኞች ፣ እ.ኤ.አ. ህዳር1 - 5 ቀን 2021 ለ 10 ሠራተኞች እንዲሁም እ.ኤ.አ. ከህዳር 22 - 26 ለ 7 ሠራተኞች "**contractors and engineering insurnce**"ስልጠና ተሰጥቷል።
- እ.ኤ.አ. ከጥቅምት 25- 29 ቀን 2021 ለ 8 ሰራተኞች ፣ እ.ኤ.አ. ከታህሳስ 6 -10 ቀን 2021 ለ 3 ሠራተኞች "**law related to insurance**" ስልጠና ተሰጥቷል።
- እ.ኤ.አ. ከጥቅምት 25- 29 ቀን 2021 ለ 9 ሰራተኞች ፣ እ.ኤ.አ. ከህዳር 22 -26 እና እ.ኤ.አ. ከታህሳስ 13- 17 ቀን 2021 ለ 7 ሰራተኞች "**motor insurance**" ስልጠና ተሰጥቷል።
- እ.ኤ.አ. ከጥቅምት 4- 8 ቀን 2021 ለ 3 ሰራተኞች "**Agriculture Insurance**" ስልጠና ተሰጥቷል።
- እ.ኤ.አ. ከጥቅምት 4- 8 ቀን 2021 ለ 6 ሰራተኞች "**principles and practice of insurance**" ስልጠና ተሰጥቷል።
- እ.ኤ.አ. ከህዳር 22- 26 ቀን 2021 ለ7 ሰራተኞች እና እ.ኤ.አ. ከታህሳስ 13- 17 ቀን 2021 ለ 6 ሰራተኞች "**marine cargo insurance** " ስልጠና ተሰጥቷል።
- እ.ኤ.አ. ከህዳር 29- ታህሳስ 1 ቀን 2021 ለ 3 ሰራተኞች "**life assurance** " ስልጠና ተሰጥቷል።
- እ.ኤ.አ. ከታህሳስ 13 -17 ቀን 2021 ለ 5 ሰራተኞች "**Risk based internal audit** " ስልጠና ተሰጥቷል።
- እ.ኤ.አ. ከታህሳስ 13- 17 ቀን 2021 ለ 8 ሰራተኞች "**marketing and customer RM** " ስልጠና ተሰጥቷል።
- እ.ኤ.አ. ከታህሳስ 20- 22 ቀን 2021 ለ 3 ሰራተኞች "**principles and practice of loss adjusting** " ስልጠና ተሰጥቷል።
- እ.ኤ.አ. ከጥቅምት 25- 29 ቀን 2021 ለ8 ሰራተኞች "**risk management and insurance** " ስልጠና ተሰጥቷል።
- እ.ኤ.አ. ከታህሳስ 27- 31 ቀን 2021 ለ 7 ሰራተኞች "**Insurance accounting** " ስልጠና ተሰጥቷል።
- እ.ኤ.አ. ከታህሳስ 27- 31 ቀን 2021 ለ 7 ሰራተኞች "**Re- insurance** " ስልጠና ተሰጥቷል።

## በITSM በኩል የተሰጠ ስልጠና

- እ.ኤ.አ. ከህዳር 24 - ታህሳስ 1 ቀን 2021 ለ3 ሠራተኞች **“end point protection 10xC: configure and protect”** በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት አማካኝነት ድርጅቱን በተሻለ አቅም እንዲያገለግሉ ለማስቻል ሥልጠና ተሰጥቷል።

*የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ከጥቅምት 1 ቀን እስከ ታህሣሥ 30 ቀን 2014 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ ለሶስት ሠራተኞች ቅጥር ያከናወነ ሲሆን ስድስት ሠራተኞች ደግሞ በጡረታ ከድርጅቱ ተሰናብተዋል።*

## *አዲስ የተቀጠሩ ሠራተኞች*



እንዳለ ሙሉ
ሲሲቲቪ ካሜራ ኦፐሬተር
ዋ/መ/ቤት
እ.ኤ.አ ታህሳስ 1 ቀን 2021



ብሩክ ፍቅሩ
ሰርቬየር
ዋ/መ/ቤት
እ.ኤ.አ ታህሳስ 1 ቀን 2021



ናፊያድ ስዩም
ሰርቬየር
ዋ/መ/ቤት
እ.ኤ.አ ህዳር 8 ቀን 2021

☞ ***የኢትዮጵያ መድን ድርጅትን አዲስ ለተቀላቀላችሁ ሠራተኞች መልካም የሥራ ዘመን ይሁንላችሁ በማለት መልካም ምኞቱን ይገልጻል !!!***

## *በጡረታ የተገለሉ የድርጅቱ ባልደረባዎች፡-*

ሀረገብዙ አይተነው
ሲኒየር ኦፕሬሽን ኦፊሰር
ምስራቅ አዲስ ዲስትሪክት
እ.ኤ.አ ጥቅምት11 ቀን 2021

ግዛቸው አሰፋ
ኢንቨስቲጌተር
ሰሜን አዲስ ዲስትሪክት
እ.ኤ.አ ጥቅምት 11 ቀን 2021

መንበረ አሰፋ
ኦፊስ አድሚኒስትሬተር
ምስራቅ አዲስ ዲስትሪክት
እ.ኤ.አ ታህሳስ 11 ቀን 2021

| | | |
|---|---|---|
| ሸዋነሽ ለማ | አለምነሽ አሰፋ | ወ/ማርያም ጌቻ |
| ሲኒየር ኦፕሬሽን ኦፊሰር | ዴስክ ክለርክ | ሲኒየር ፋይናንስ ኦፊሰር |
| ሰሜን አዲስ ዲስትሪክት | ምዕራብ አዲስ ዲስትሪክት | ሰሜን አዲስ ዲስትሪክት |
| እ.ኤ.አ ህዳር 10 ቀን 2021 | እ.ኤ.አ ህዳር 12 ቀን 2021 | እ.ኤ.አ ታህሳስ 10 ቀን 2021 |

- ***የኢትዮጵያ መድን ድርጅትን በጡረታ ለተሰናበታችሁ ሠራተኞች መልካም የእረፍት ጊዜ እንዲሆንላችሁ ልባዊ ምኞቱን ይገልፃል!!!***



***የኢትዮጵያ መድን ድርጅትን የዜና መድን መጽሔት ስላነበባችሁ ከልብ እያመሰገንን ስለ ዜና መጽሔቷም ሆነ አጠቃላይ ስለ ድርጅቱ ያላችሁን አስተያየት በድርጅቱ ኢ-ሜይል አድራሻ eic.mdxvs@eic-et.com / bdrm@eic-et.com ወይም በፖስታ ሣ.ቁ. 2545 ለኢንተግሬትድ ኮሙዩኒኬሽን ቡድን በሚል እንድትልኩልን በአክብሮት እንጠይቃለን።***